የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ተጠሪ ጽ/ቤት
**KINIJIT North America Support Office**
www.Kinijit.org

# መግለጫ

# ትግላችንና መስዋዕትነታችን በገጸ በረከትነት አይቀርብም

ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም እንዲሉ የዘንድሮዉ ዓመት ጉድ ይዞልን መጥቷል:: የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ ልዑክ መሪ ነኝ የሚሉት የቅንጅት ተ/ም/ፕሬዚደንት ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ኦክቶበር 21 ቀን 2007 ዓ.ም ሚኒያፖሊስ ከተማ ላይ ለተሰበሰበ ሕዝብ ቅንጅትን እንደ ጥፋተኛ በመቁጠር በቅንጅት ስም የትግራይን ተወላጆች ይቅርታ መጠየቃቸዉን ሰማን::

ለይቅርታዉ ያቀረቧቸዉ ምክንያቶች:-

1 አቶ በድሩ አደም በሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ኢህአዴግን ወደ መጣበት እንመልሰዋለ በማለታቸው፣

2. ከእርሳቸዉ ቁጥጥር ዉጭ በሆነዉ የቅንጅት ድረ ገጽ Kinijit.org ላይ የወጡ ጽሁፎች የትግራይ ተወላጆችን በማስቀየማቸው የሚሉ ናቸው::
በእኛ በኩል ይህ የወ/ሪት ብርቱካንና የቡድናቸው አቋም ምክንያታዊ ያልሆነና በሀቅ ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ ድብቅ አጀንዳን ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ለእርምጃቸዉ የመሰረት ድንጋይ እንዲሆን የታለመ እንዳይሆን በእጅጉ እንሰጋለን:: የቅንጅት አባልና ደጋፊ እንዲሁም መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብም ይስጋ::

እስኪ የቀረቡትን ምክንያቶች ተራ በተራ እንያቸዉ:

- አቶ በድሩ « ኢሕአዴግን ወደ መጣበት እንመልሰዋለን» ያሉበትን የልባቸዉን አገላለጽ በወቅቱ ለሕዝብ በጋዜጦች በኋላም ለፍ/ቤት «ኢሕኢዴግ ከሥልጣኑ ይዉረድ» ለማለት እንደተጠቀሙበት በአግባቡ አስረድተዋል: የአንድ ሰዉ መልዕክት ደግሞ መተርጎም ያለበት መልዕክቱን ባስተላለፈዉ ሰዉ እንጂ በተቀናቃኙ ሊሆን አይችልም:: ታዲያ በምርጫ ዉድድር ወቅት ኢኢሕአዴግ

8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD. 20910
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090,
Email: KinijitUSA@Kinijit.org

ከሥልጣን ይዉረድ ማለት ምን ወንጀል አለበት? እና ይቅርታ ጥያቄን ምን አመጣው ?

- አቶ በድሩ በዚሁ ጉዳይ ክስ ተመስርቶባቸዉ ተገቢዉን ማስረጃ አቅርበዉ ፍ/ቤቱም በነፃ ለቋቸዋል:: ታዲያ ይቅርታን ምን አመጣዉ?
- በቅንጅት የተፈጸመ ስህተት በጭራሽ የለም:: ስህተት ተፈጽሟል እንኳን ቢባል ይቅርታ መጠየቅ ያለበት ኢሕአዴግ እንጂ የትግራይ ተወላጆች ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ የለም:: ምክንያቱም ምንም እንኳን ኢሕአዴግን ማን ይመራዋል የሚለዉ አጠያያቂ ቢሆንም ራሱ ኢሕአዴግ « ለአማራዉ፣ለትግሬዉ፣ ለደቡቡ፣ ለኦሮሞዉ ባጠቃላይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየሠራሁ ነዉ» እያለ እየለፈፈ ባለበት ሁኔታ በምን ሂሳብ ነው የትግራይ ተወላጆችን በሙሉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ነጥለዉ አፍቃሪ የኢሕአዴግ ያደረጓቸዉ?
- መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢሕአዴግ የግፍ አገዛዝ ምሬቱን በአንድ ድምጽ በሚያሰማበት በአሁኑ ወቅት የትግራይ ተወላጆችን ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ በመነጠል አፍቃሪ ኢሕአዴግ አድርጎ ለማቅረብ ለምን ተሞከረ? የአዞ እንባ? ወይስ ማንን ለማስደሰት ታልሞ?
- ወ/ት ብርቱካን «የቅንጅት ተ/ምክትል ፕሬዚዳንት ነኝ» እያሉ ነዉ ታዲያ እንዴት ቅንጅት የመላው ኢትዮጵያዊ፣ የአንድነት የዲሞክራሲና የነጻነት ተስፋ መሆኑን አጡት? በእርግጥ እርሳቸዉ ቅንጅትን የተቀላቀሉት ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ በመሆኑ ብዙ እንዲያውቁ ባይጠበቅም፣ ቅንጅት በሽዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች አባላት እዳሉት ማወቅ ነበረባቸዉ:: በትግራይ ቢሮዎችን ከፍቶ በስፋት ይንቀሳቀስ እንደነበረም ማወቅ ነበረባቸዉ:: በግንቦቱ ምርጫ ወቅት በትግራይ ለተወካዮችና ለክልል ም/ቤቶች ተወዳዳሪዎቹን አቅርቦ እንደነበረም ማወቅ ግዴታቸዉ ነበር:: በአዲስ አበባ ለክልልና ለተወካዮች ም/ቤት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ተመራጮችስ እንደነበሩን እንዴት አጡት? በአሁኑ ወቅት ከጎናቸዉ ቁጭ ብለዉ ስብሰባ እየመሩ ያሉትንና በወህኒ ቤት አብረዋቸዉ ግፍና መከራ የተቀበሉትንስ የትግራይ ተወላጅ እንዴት እንደሌሉ ቆጠሩአቸዉ?
- ወ/ሪት ብርቱካን የቅንጅት ልሣን የሆነዉን ድረ-ገፅ Kinijit.org ን አዉግዘዉ «ይቅርታ» ጠይቀዉለታል:: ይህ ድረ-ገጽ የድርጅቱን ወቅታዊ አቋሞች ከማንጸባረቁ በስተቀር በትግራይ ተወላጅ ወንድሞቻችን ላይ ያደረገዉ አፍራሽ ቅስቀሳ የለም::
- ሊኖርም አይችልም::

8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD. 20910
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090,
Email: KinijitUSA@Kinijit.org

- እርሳቸዉና ቡድናቸዉ በእርግጥ ከልብ የትግራይ ተወላጆችን ይቅርታ ለመጠየቅ ከተነሳሱ መጠየቅ ያለባቸዉ እነርሱ የሚቆጣጠሩአቸው በእጅ አዙር የሚያስተዳድሩዋቸዉ በፋይናንስ የሚደግፉአቸው በየአህጉሩ ያሰማሩዋቸዉ ዘረኛ ከድሬዎቻቸዉ በፓልቶክና በአንዳንድ ድረ-ገጾች ሲነዙት ስለከረሙት ዘረኛና ከፋፋይ መግለጫዎች መሆን አለበት:: የቅንጅት አመራር በወህኒ በነበረበት በተለይ ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ሰጠ በተባለበት ሰሞን የእርሳቸዉና የቡድናቸው ጋሻ ጃግሬዎች ቀንደኛ ካድሬዎቻቸውን ጨምሮ ይሰጧቸዉ የነበሩትን ዘረኛ መግለጫዎች እርሳቸው እንደሚያዉቁት አንጠራጠርም::
- ይህ የእርሳቸዉና የቡድናቸዉ አቋም ሁለት ዐላማዎች እንዳሉት ያመለክታል:: አንደኛዉ ዛሬ በአፍራሽና መስረተቢስ አሉባልታ ከትግል ሊያገሏቸው ሌት ከቀን የሚጥሩት ኢንጂነር ኃይሉ ሻወልንና እርሳቸውን የሚደግፉ ቡድኖች፣ ግለሰቦችና ተቋማትን ከትግራይ ተወላጆች ጋር በማጋጨት ትርፍ ይገኛል ብሎ ከማለም የመጣ የዘቀጠ አስተሳሰብ ነዉ::
- ሁለተኛዉ ኢንጂነር ኃይሉና ተከታዮቻቸዉ የትግራይ ተወላጆችን አይወዱም የሚል መሰረተ ቢስ ቅስቀሳ በማካሄድ ከገዥዉ ፓርቲ በተለይም ከህወሀትና ከመንግስት ባለስልጣናት ድጋፍ ለማግኘት የታለመ ቅንጂትን በገጸ በረከትነት የማቅረብ እርምጃ ነዉ ማለት ይቻላል::
- ኢሕአዴግ ቅንጅትን በዘር ማጥፋት ወንጀል በመክሰስ አመራሩን ለወህኒ ዳርጎት የቆየዉ ዛሬ እነ ወ/ት ብርቱካን የሚያናፍሱትን ዓይነት መሠረተ ቢስ ዉንጀላ በማቅረብ ነበር:: ዛሬ ደግሞ እሳቸዉና ቡድናቸዉ ኢሕአዴግ የከሰረበትን መፈክር በማንሳት ዳግም ቅንጂትን በዘረኝነት እየከሰሱ ነው:: መክሰስ ብቻ አይደለም ጥፋተኝነቱንም አምነው በይፋ ይቅርታ ጠይቀዉለታል ::
ይህ የይቅርታ ጥያቄ በሰኔ 1 ቀን 96 እና በጥቅምት 22 / 97 ሰሞን በሰላማዊ መንገድ ተቃዉሞዉን ባሰማዉ ህዝብ ላይ የተፈጸመዉን ግድያ፣ አካል ማጉደል፣ ንብረት ማዉደምና እሥራት በቅንጅት ዘረኛነት ሳቢያ የመጣ እንጂ የኢሕአዴግ ጥፋት እንዳልሆነ ለማስመሰል የታቀደው ሴራ የመጀመሪያው ምዕራፍ ስለመሆኑ ጠቋሚ ነዉ::

- ኸረ ለመሆኑ ይህን አቋማቸዉን ለምን የመጀመሪያ ስብሰባቸዉን ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ሲያካሂዱ አላደረጉትም? አቋማቸውን በተልኮአቸዉ መጀመሪያ ላይ ይፋ ያላደረጉት በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ተቃውሞ እንደሚያጋጥማቸው በማሰብ ነው:: ይህን አፍራሽ አቋማቸውን በውስጣቸው ቋጥረው ከሰነበቱ በኋላ በመጨረሻ ላይ በአደባባይ የተናገሩበት ምክንያት ወደ

8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD. 20910
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090,
Email: KinijitUSA@Kinijit.org

አገር ሲመለሱ አንድን ቡድን በጸረ የትግራይ ተወላጅነት በመወንጀልና በገጸ በረከትነት በማቅረብ በሥልጣን የሰከሩ ዘረኞችን ታማኝነት ለማትረፍ እንዳይሆን እንሰጋለን።

- ቀደም ሲል ወ/ሪት ብርቱካን በቡድናቸዉ ስም በአሜሪካ ኮንግረስ ፊት ቀርበዉ «በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ቁጥር 100 ብቻ ነዉ» ብለዉ የመሠከሩት ከልባችን ሳይወጣ ዛሬ ይህን የመሰለ አድራጎት መፈጸማቸዉ በእጅጉ አሳዝኖናል።

ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ እንዲሉ ይህ ከኢሕአዴግ የዘረኝነት ፖሊሲ በባሰ መልኩ የተጀመረ አፍራሽ እንቅስቃሴ አገራችንን፣ ሕዝባችንና ትግላችንን በእጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን። እኛ ዛሬም ቅንጅት አነድነት ነዉ፣ ቅንጅት ፍቅር ነዉ፣ ቅንጅት ኢትዮጵያዊነት ነዉ እንላለን። ይህ ጽኑ አቋማችን ምን ጊዜም እንደማይሸረሸር ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ እናረጋግጣለን። በዚህ አጋጣሚ ጊዜያዊ ትርፍ በመሻት በኢትዮጵያችንና በትግላችን ላይ እንደማንደራደር ለመላዉ ሕዝብና ለወዳጆቻችን ደግመን እናረጋግጣለን።

***ቅንጅት አንድ ነዉ!***
***ኢትዮጵያም አንድ ናት!***
***በትግላችንና በመስዋዕትነታችን ላይ አንደራደርም!***

*ጥቅምት 16 ቀን 2000 ዓ.ም*
*ዋሽንግተን፣ ዲሲ*

**የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጭ ም/ቤት**

**8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD. 20910**
**Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090,**
**Email: KinijitUSA@Kinijit.org**